Australian Government

Department of Home Affairs

# Information about DNA testing for visa and citizenship applicants

# ለቪዛና ለዜግነት አመልካቾች ስለዲኤንኤ (DNA) ምርመራ የቀረበ መረጃ

Form

1259i AMH

AMHARIC

## ስለዲኤንኤ (DNA)

ዲኤንኤ/DNA (ዲኦክሲሪቦኒዩክሊክ አሲድ) በእያንዳንዱ የሰውነት ሕዋስ (ሴል) ውስጥ የሚገኝ ጀነቲከ ማቴሪያል ነው። ለምሳሌ፡ በደም፣ በምራቅ፣ በቆዳና በፀጉር ውስጥ ይገኛል። ሁሉም ሰው ዲኤንኤ አለው። አንድ ሰው የራሱ የሆነ ዲኤንኤ ከወላጆቹ ይወርሳል። ስለዚህም የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች ተመሳሳይ የሆነ ዲኤንኤ ይጋራሉ።

## የዲኤንኤ ምርመራ

የዲኤንኤ ምርመራ ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ሰዎች የጀነቲክ ማቴሪያል ወስዶ በማነጻጸር የስጋ ዝምድና እንዳላቸው ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ ነው። ለምርመራ የሚሆነው ጀነቲክ ማቴሪያል ብዙውን ግዜ የሚወሰደው ከአፍ ውስጥ በጥጥ ተጠርጎ ወይም ከደም ናሙና ነው።

## ለምንድነው አንዳንድ አመልካቾች የዴኤንኤ ምርምራ እንዲያደርጉ የሚጠየቀው፡

የአገር ጉዳዮች መምሪያ/Department of Home Affairs (ከአሁን በኋላ መምሪያው ይባላል) የስጋ ዝምድና አለን የሚሉ ሰዎች እውነተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚጠቀምበት አንዱ ዘዴ የዲኤንኤ ምርመራ ነው። እንደተለመደውም ሌሎች መረጃዎች ለምሳሌ፤ የልደት ምስክር ወረቀት ወይም የቤተሰብ ሰነዶች ይታያሉ። ይሁን እንጂ የዲኤንኤ ምርመራ የሚደረገው የስጋ ዝምድና አለን የሚሉ ሰዎች የሚያቀርቡት ሰነድ በቂ ካልሆነና ወይም ምንም ማስረጃ ማቅረብ ካልቻሉ የሚደረግ ምርመራ ነው።

ባለጉዳዮች የስጋ ዝምድና እንዳላቸው ለማሳየት ያቀረቡትን ማስረጃ መምሪያው ካላመነበት፡ እውነቱን ለማረጋገጥ ሲል የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደረጉ ሊጠይቅ ይችላል።

ቪዛ ወይም የአውስትራሊያ ዜግነት ለማግኘት ሲያመለክቱ የመመዘኛ ነጥቦችን ለማሟላት፡ የስጋ ዝምድና እንዳለ ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ይጠየቁ ይሆናል። የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት በትውልድ ዝምድና እንዳለ ያረጋግጣል፤ ለምሳሌ፤ በወላጆችና በልጆች ወይም በወንድምና በእህቶች መካከል ያለውን የስጋ ዝምድና ለማረጋገጥ ይቻላል።

## የዲንኤ ምርመራ ማድረግ ግዴታ አይደለም

የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት ለምን ተግባር እንደሚውል ካወቁ አላደርግም ማለት ይችላሉ።

የዲኤንኤ ምርመራ አድርጉ ብሎ የሚያስገድድ ሕግ የለም። ሌላ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እንጂ ግዴታ አይደለም፤ የልደት ምስክር ወረቀት ካልኖረ የሚደረግ ሌላ አማራጭ ነው። የዲኤንኤ ምርመራ ለማድረግ ከወስኑ፣ መምሪያው የሚፈልገውን ለማሟላት ምን ማድረግ እንዳለቦት ከመምሪያው መግለጫ ይሰጦታል። መምሪያው ከሚፈልጋቸው ነገሮች ውጪ የሚመጡ የምርመራ ውጤቶች ተቀባይነት ላያገኙ ይችላሉ።

የዲኤንኤ ምርመራ ላለማድረግ ከወሰኑ፡ ባቀረቡት የቪዛ ወይም በትውልድ የአውስትራሊያ ዜግነት ማመልከቻ ላይ መምሪያው የሚሰጠው ውሳኔ በቀረቡለት ሌሎች መረጃዎች ላይ ብቻ ተመርኩዞ ይሆናል።

## ለዲንኤ ምርመራ የሚከፈለው

የስደተኛ ቪዛ ወይም በትውልድ የአውስትራሊያ ዜግነት የሚጠይቁ አመልካቾች ሁሉ ለዲኤንኤ ምርመራ የሚወጣውን ወጪ መክፈል ያለባቸው እነርሱ ናቸው።

የስደተኛ ቪዛ አመልካቾች ለዲኤንኤ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ መምሪያው ይሸፍናል። ይሁን እንጂ የሰብአዊ ፕሮግራም (ስፔሻል ሂውማኒተሪያን ፕሮግራም) አመልካቾች የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደርጉ ከተጠየቁ ለዲኤንኤ ምርመራው የሚፈለገውን ወጪ ሁሉ እነርሱ መክፈል አለባቸው።

## ምክክር

የዲኤንኤ ምርመራ ለማድረግ ከመወሰኖ በፊት ከጤና ባለሙያዎች ወይም ከዶክተሮች ጋር ምክክር (ካውንስሊንግ) ማድረግ ይችላሉ። የዲኤንኤ ምርመራ ውጤቱ ከታወቀ በኋላም እንኳ ቢሆን ምክር መጠየቅ ይችላሉ።

**ማስታወሻ፡** ለምክክር (ለካውንስሊግ) የሚወጣውን ወጪ የሚከፍሉት እርሶኖት።

## የዲንኤ ምርመራ ውጤት ምንን ያሳያል

የወላጅና የልጅ ዲኤንኤ ምርመራ ውጤት በመካከላቸው ያለውን የስጋ ዝምድና (መዋለድን) ያሳያል።

ብዙውን ጊዜ የዲኤንኤ ምርመራ አመልካቾች ያላቸውን የስጋ ዝምድና ያረጋግጣል።

የዲኤንኤ ምርመራ አንዳንድ ግዜ ደግሞ ሌሎች የቤተሰብ አባሎቾ ያላቸውን የስጋ ዝምድና በማያሻማ መንገድ ማሳየት አይችል ይሆናል። ውጤቱ ግልጽ ካልሆነ ላቦራቶሪው በዚያ ላይ ማብራሪያ ይስጥበታል።

## የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት ለምን ተግባር እንደሚውል

ለመምሪያው የሚሰጠው የዲኤንኤ የምርመራ ውጤት በጥብቅ ለኢሚግሬሽን ጉዳይ ብቻ ይውላል።

## ስለ ግላዊነት አጠባበቅ ጠቃሚ መረጃ

የ *Privacy Act 1988 (ግላዊነት አንቀጽ ሕግ 1988 ዓ.ም)* 13 የአውስትራሊያ ግላዊነት መሰታዊ ስርዓቶችን እንደያዘ፤ ይህም በመምሪያው ግላዊ መረጃን ለመሰብሰና ለመያዝ መንገድን ይቆጣጠራል። መምሪያው የግል መረጃን እንዴት መሰብሰብ፣ መጠቀም እንዳለበትና መረጃዎችን ለራሱ ቁልፍ የሆነ ሥራ ተግባር ሲል ሌላ አካል ጠቃሚ መረጃዎቸን ስሰማውጣት በቅጽ 1442i *Privacy notice (የግላዊነት ማሳወቂያ)* ላይ መረጃ ማግኘት ይቻላል። ስለ የመምሪያ መረጃ ኣያያዝ ተግባር ሥራ (ለቅጽ 1442i ያካተተ) አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት የመመሪያ ግላዊነት ፖሊሲ በድረገጽ **https://www.homeaffairs.gov.au/access-and-accountability/our-commitments/privacy** ላይ ገብቶ ማግኘት ይቻላል።

የዲኤንኤ መመርመሪያ ላቦራቶሪዎች የዲኤንኤ ውጤቱን ለመምሪያውም ሆነ እርስዎን ስፖንሰር ላደረገው ሰው ወይም ድርጅት ከማሳወቃቸው በፊት ከእርሶ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

የወሰዱት የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት በግል ሚስጥር እንዴት እንደሚጠበቅ ለማወቅ ከፈለጉ፡ የዲኤንኤ ምርመራ ከአደረገሎት ላቦራቶሪ ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

## ዲኤንኤ የሚመረምሩ ላቦራቶሪዎች

መምሪያው የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደርጉ ከጠየቅዎት፡ ምርመራውን ለማካሄድ የሚመርጡት ላቦራቶሪ ለቤተሰብ የምርመራ ሕግ በሚያወጣው፣ የመርማሪ ባለስልጣን ብሔራዊ ማኅበር [National Association of Testing Authorities, Australia (NATA) for family law] እውቅና የተሰጠውና፣ ከአውስትራሊያ ውጪ ከሆኑ ደግሞ እንደየሀገሩ አግባብ መምሪያው የሚፈልገውን ዓይነት የዲኤነኤ ምርመራ ማሟላት የሚችል ላቦራቶሪ መሆን አለበት።

**ማስታወሻ፡** ተቀባይነት ላገኘ የዲኤንኤ ናሙና ስብሳቢውን እራስዎት መምረጥ ይኖርቦታል።

የዲኤንኤ መመርመሪያ ላቦራቶሪ እንዴት መምረጥ እንደሚችሉ ከታች በደረጃ 3 ያለውን ይመልከቱ። በደረጃ 5 ደግሞ የዲኤንኤ ናሙና ስብሳቢውን እንዴት መምረጥ እንደሚችሉ ይገልጻል።

## የዲኤንኤ ምርመራ ሂደት

የዲኤንኤ ምርመራ ሂደት የሚከተሉትን ደረጃዎች ይይዛል፤

1. የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደርጉ መምሪያው ደብዳቤ ይልክሎታል። በደብዳቤውም ሰለዲኤንኤ ምርመራ፣ የዲኤንኤ ምርመራ ሂደት፣ የዲኤንኤ መመርመሪያ ላቦራቶሪንና የዲኤንኤ ናሙና ስብሳቢን እንዴት እንደሚመርጡ ለማሳወቅ መረጃ ይሰጦታል።
2. በዲኤንኤ ምርመራው መቀጠል ከፈለጉ መወሰን ይገባዎታል። አልያም ደግሞ ከጤና ባለሙያ ወይም ከዶክተር ጋር ምክክር ማድረግ ይችላሉ። ይሁን እንጂ የዚህን ወጪ መክፈል ያለቦት ራስዎ ኖት።

   የዲኤንኤ ምርመራ **ላለማድረግ** ከወሰኑ ግን፡ የስጋ ዝምድና ስላለኝ ቪዛ ወይም ዜግነት ይሰጠኝ ብለው ለሚያቀርቡት ማመልከቻ፡ መምሪያው ውሳኔውን የሚሰጠው፡ በወቅቱ በቀረቡለት መረጃዎቾ ላይ ብቻ ተመርኩዞ ይሆናል።

© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2020

3. በ**ዲኤንኤ** ምርመራው ለመቀጠል ከወሰኑ፣ ምርመራውን ለማካሄድ የሚመርጡት የ**ዲኤንኤ** መርማሪ ላቦራቶሪ፡ ለቤተሰብ የምርመራ ሕግ በሚያወጣው፣ የመርማሪ ባለስልጣን ብሔራዊ ማኅበር [National Association of Testing Authorities, Australia (NATA) for family law] እውቅና የተሰጠው ሲሆን ከአውስትራሊያ ውጪ ከሆኑ ደግሞ እንደየሀገሩ አግባብ መምሪያው የሚፈልገውን የ**ዲኤነኤ** ምርመራ ዓይነት ማሟላት የሚችል ላቦራቶሪ መሆን አለበት። ላቦራቶሪ ለመፈለግ፤

   - በNATA ድረ-ገጽ ላይ መግባት **www.nata.com.au/accredited-facility**
   - እውቅና ያላቸውን  የምርመር ላቦራቶሪዎች ለመፈለግ 'Parentage Testing' የሚለውን ቃላት በ 'Keyword' የመፈለጊያ ማሳያ ላይ በማስገባት ከዚያም 'SEARCH' የሚለውን መጫን እና
   - የመረጡት ላቦራቶሪ መምሪያው የሚፈልገውን ዓይነት ማሟላት እንደሚችል በእርግጠኛነት ለማወቅ ላቦራቶሪውን ማነጋገር ይኖርቦታል።

   **ማስታወሻ:** እርስዎ የስደተኛ ቪዛ አመልካች ከሆኑ ለርስዎ የሚሆን ላቦራቶሪ ይመረጥልዎታል።

4. አንድ ግዜ የ**ዲኤንኤ** ምርመራ የሚያደርጉበትን ላቦራቶሪ ከመረጡ በኋላ ከላቦራቶሪው ጋር ተገናኝተው ቀጠሮ መያዝና ለ**ዲኤንኤ** ምርመራው የሚጠየቀውን ወጪ ለመክፈል ከላቦራቶሪው ጋር በመነጋገር ማመቻቸት ይኖርቦታል።

   በተጨማሪም ደግሞ የዲኤንኤ መሰብሰቢያ ስምምነት መግለጫ/1528 *DNA Collection Statutory declaration* ቅጽ እና የዲኤንኤ መሰብሰቢያ ማካተቻ ወረቀት /1527 *DNA Collection Cover sheet* ቅጽ እንዲልኩላቸው ከፈለጉ ከላቦራቶሪው ጋር ሆነው ማጣራት አለብዎት ስለዚህ ቅጹን መሙላት፤ መፈረም እንደሚችሉና አስፈላጊ ወደሆነው የቪዛ ሂደት ማካሄጃ ቢሮ ቅጾችን መላክ ይችላሉ። ቅጽ 1528 እና ቅጽ 1527 በመምሪያው ድረ ገጽ **www.homeaffairs.gov.au/allforms** ላይ ይቀርባሉ።

   **ማስታወሻ፡** ምርመራውን ያካሄዱት ከአውስትራሊያ ውጪ ከሆነ፡ መምሪያው ከላቦራቶሪው ጋር በቀጥታ ለመገናኘት ያመቻቸ ከሆነ፡ እርሶ የስምምነት መግለጫ የሕግ ሰነዱ (statutory declaration template) ተሞልቶ እንዲፈረምበት ወደዚያ ላቦራቶሪ መላክ አያስፈልጎት ይሆናል።

5. ለ**ዲኤንኤ** ምርመራ ለመስጠት ናሙና ሰብሳቢ መርጠው ማዘጋጀት ይኖርቦታል። ናሙና መውሰድ እንዲችሉ ቀጠሮ ለማመቻቸት የ**ዲኤንኤ** ምርመራውን ለሚያካሂደው ላቦራቶሪ አድርሻዎን መስጠት ይኖርቦታል። የ**ዲኤንኤ** ናሙና ሰብሳቢውን ለመምረጥ፤

   - ከአውስትራሊያ ውጪ ከሆኑ - ጉዳዮትን የያዘው የውጪ ሀገር ጽ/ቤታችን በአካባቢው እውቅና ከተሰጣቸው የ**ዲኤንኤ** ናሙና ሰብሳቢዎች ውስጥ እንዲመርጡ ዝርዝሩን ምርመራ እንዲያደርጉ ከሚጠይቀው ደብዳቤ ጋር አብሮ ይልክሎታል።
   - በአውስትራሊያ ውስጥ ከሆኑ - በአውስትራሊያ ውስጥ የሚገኝ ናሙና የሚሰበስብ የፓቶሎጂ ማዕከል መምረጥ ይኖርቦታል (ወይም፣ የፓቶሎጂ ናሙና ሰብሳቢ ማዕከል ብዙውን ግዜ በአካባቢዎት ባይታጣም፣ ካላገኙ ግን የህክምና ዶክተር መጠቀም ይችላሉ)፡ የሚመርጡትም የ**ዲኤንኤ** ናሙና ስብሳቢ ለቤተስብ ሕግ ጉዳይ እንደሚደረገው ሁሉ የመምሪያውን ፍላጎት የሚያሟል መሆን አለበት።

6. ምንም ነገር ግን ካልሰሩ፣ ላቦራቶሪው ለናሙና መሰብሰቢያ መሳሪያ ይልክሎታል፡ አስፈላጊ ከሆነም ደግሞ ተሞልቶ የተፈረመበትን የስምምነት መግለጫ የሕግ ሰነድ (statutory declaration) በቀጥታ ወደሚከተለው ክፍል ይልካል፤

   - ምንም ያደረጉት ነገር ካልኖረ፣ ላቦራቶሪው ለናሙና መሰብሰቢያ መሳሪያ ይልክሎታል፡ አስፈላጊ ከሆነም ደግሞ ተሞልቶ የተፈረመበትን የስምምነት መግለጫ የሕግ ሰነድ (statutory declaration) በቀጥታ እርሶ ወደመረጡት የ**ዲኤንኤ** ናሙና ሰብሳቢ ይላካል)፣ ወይም
   - አውስትራሊያ ውስጥ ከሆኑ - ለመረጡት የ**ዲኤንኤ** ናሙና ስብሳቢ ይላካል።

7. ከዚያም የ**ዲኤንኤ** ምርመራውን የሚያካሂደው ላቦራቶሪ ከእርሶና ከሌሎቹ የ**ዲኤንኤ** ምርመራ ከሚያደርጉ ሰዎች ናሙና ለመውሰድ ከእርሶ ጋር በመነጋገር ቀጠሮ ይይዛል። ብዙውን ግዜ ናሙና ከአፍ ውስጥ በጥጥ ተጠርጎ ይወሰዳል ወይም የደም ጠብታ ይወሰዳል።

   ከአውስትራሊያ ውጪ ምርመራ የሚደረግላቸው ተመርማሪዎች ሁሉ ናሙና ሲሰጡ የመምሪያው ተወካይ **የግድ** በቦታው መገኘት ይኖርበታል። አልፎ አልፎም በአውስትራሊያ ውስጥ ናሙና ሲወሰድ ታዛቢ ምስክር ሊያስፈልግ ይችላል።

   የመምሪያውን መጠይቅ የማያሟሉ የ**ዲኤንኤ** ምርመራዎች ተቀባይነት ላያገኙ ይችላሉ። (በአውስትራሊያ ውስጥ በሕግ የታወቁ የ**ዲኤንኤ** ምርመራ ውጤቶች ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ)።

8. የዲኤንኤ ናሙና በሚሰጡበት ወቅት፤ በመምሪያው ድረ ገጽ ላይ ለቀረበው ቅጽ 1526 *የዲኤንኤ መሰብሰቢያ ስምምነት መግለጫ/1526 DNA Collection Consent declaration* ሞልተው መፈረም ይኖርብዎታል (ይህንን ለዲኤንኤ ናሙና ሰብሳቢ ለማሳየት ይዘው መሄድ አለብዎት)። የስምምነት መግለጫ ያስፈለገው የርስዎን ዲኤንኤ ምርመራ ውጤት ለመምሪያው ለማሳየት የርስዎን ፈቃድ ለማግኘት ነው። ናሙና የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ናሙና በሚሰጥበት ወቅት ይህንን የስምምነት ፕሮፎርማ ሞልቶ ለሚከተሉት ክፍሎች መስጠት አለበት፤

   - ከአውስትራሊያ ውጪ ከሆኑ - ከመምሪያው የተላከ ታዛቢ የተዘጋጀውን የስምምነት መስጫ ፕሮፎርማ እና ናሙና በአንድ ላይ እድርጎ ለሚመለከተው የ**ዲኤንኤ** መርማሪ ላቦራቶሪ ይልካል (ማስታወሻ፡ አልፎ አልፎም ናሙና ሰብሳቢው ይህንን ሊስራ ይችላል□፣ ወይም
   - በአውስትራሊያ ውስጥ ከሆኑና ከመምሪያው የተላከ ታዛቢ ካልኖረ - የ**ዲኤንኤ** ናሙና ሰብሳቢው የተዘጋጀውን የስምምነት መስጫ ፕሮፎርማ እና ናሙናውን በአንድ ላይ አድርጎ ለሚመለከተው የ**ዲኤንኤ** መርማሪ ላቦራቶሪ ይልካል።

   የ**ዲኤንኤ** ምርመራ ውጤት ለእርሶና ለመምሪያው ይላካል፡ ብዙን ግዜ ይህ የሚሆነው የ**ዲኤንኤ** መርማሪ ላቦራቶሪው ናሙናዎች ሁሉ ከደረሱት ከ14 ቀናት በኋላ ነው።

9. የ**ዲኤንኤ** ምርመራ ውጤት ያልተጠበቀ ማለትም የስጋ ዝምድና መኖሩን የማያሳይ ከሆነ (ለምሳሌ፡ “ከእናት” ወይም “ከአባት” የተወሰደ የምርመራ ውጤት ወላጅ አለመሆናቸውን ካሳየ) አማካሪ ለማዋየት ይፈልጉ ይሆናል። ለዚሁ ተግባር በአውስትራሊያ መንግስት የተመደበ ዶክተር ስላለ ከእርሱ ጋር መወያየት ይችላሉ።

   **ማስታወሻ፡** ይህንን የመሳሰሉ አገልግሎቶች ማግኘት እየፈለጉ አማካሪ ዶክተር ግን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ አስቀድሞ ካልተነገርዎት፣ ዝርዝር መረጃ የቪዛና የዜግነት ማመልከቻ ጉዳይን ከሚመለከተው የመምሪያው ጽሕፈት ቤት ማግኘት ይችላሉ።

## ይህን መረጃ በተለያየ ቋንቋ ማንበብ ይችላሉ

ይህ መረጃ በተጨማሪም በሚከተሉት ቋንቋዎች ተተርጉሞ ይገኛል፤

- አማርኛ፤
- አርብኛ፤
- ዳሪ፤
- ፈረንሳይኛ፤
- ሃክሃ ቺን (የቺን አስተዳደር ግዛት– በርማ)
- (ኩርማንጂ)
- ኩርዲሽ (ሶራኒ)
- ቻይነስ (ሲምልልፋይድ)
- ሶማሊኛ፤
- ታገሎግ፤
- ቬትናምኛ።

## ስለዲኤንኤ ምርመራ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ

እርሶም ሆኑ ዘመድዎ የ**ዲኤንኤ** ምርመራ እንድታደርጉ ከተጠየቃችሁና ያልገባዎትን ነገር ለማወቅ፤ ወይም ስለ**ዲኤንኤ** ምርመራ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት ከፈለጉ ምርመራ እንዲያደርጉ የጠየቅዎትን የመምሪያውን ክፍል ያነጋግሩ ወይም የመምሪያውን ድረገጽ **www.homeaffairs.gov.au** ይጎብኙ።

| | |
|---|---|
| ***የሸፋን ገጽ*** | **www.homeaffairs.gov.au** |
| ***አጠቃላይ የመረጃ መስመር*** | በስልክ ቁጥር **131 881** በአውስትራሊያ የስራ ሰዓት በመደወል ኦፕሬተር ያነጋግሩ (ከስራ ሰዓት ውጪ ደግሞ የተቀረጸውን ድምጽ በማዳመጥ መረጃ ያገኛሉ)። ከአውስትራሊያ ውጪ ከሆኑ ባቅራቢያዎ የሚገኘውን የአውስትራሊያ መልእክተኛ ጽ/ቤት (Australian mission) ያነጋግሩ። |


© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2020